# ጥላ

## ዋና ስራ አስኪያጅ — General Manager
መስፍን አብርሃ — Mesfin Abraha

## ዋና አዘጋጆች — Editor In Chiefs
እየሩሳሌም ሱሞሮ — Eyerusalem Sumoro
ብሩክ ገ/መስቀል(ካርቱኒስት) — Biruk G/Meskel(Cartoonist)
ዳዊት ፋንታ — Dawit Fanta

## አዘጋጆች — Editors
ዮሃንስ ሳምሶን — Yohanes Samson
ብሩክ ሃይሉ — Biruk Hailu

## ፅሁፍ አስተባባሪዎች — Coordinators
ዮሴፍ ክፍሌ — Yosef Kifle
ኤደን ዳዊት — Eden Dawit
ዳንኤል ፋንታ — Daneil Fanta
ህይወት ጥላሁን — Hiwot Tilahun
ወልደኪሮስ አስፋው — Weldekiros Asfaw

## የኮምፒዩተር ፅሁፍ ቅንብር — Computer Graphics
ሩት ተሰማ — Rut Tesema
ህሊና ዳዊት — Hilina Dawit
ዮናስ ተስፋይ — Yonas Tesfay

**የጥላ መፅሄት አድራሻ/Tila Magazine Address**
Mesfin Abraha
Löhrgasse 4
36251 Bad Hersfeld
Email:- tilamagazine@yahoo.de
Web-Site:- tilamagazine.yolasite.com
Tel.No.:- 015222195567,017659384456
017668830082, 017671668780

# ማውጫ

ገጽ


ሰው ጥራ ቢሉት እራሱ መጣ 7
ጨካኙ የወያኔ መንግስት 7
ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም 7
በጋራ እንታገል 7
የታሪክ ተጠያቂዎች አንሁን! 8
ለውጥ የለም እንጂ ...... 8

ህፀፀ ወያኔ! 8
በጋራ ተሳትፏችን የወያኔ የይምሰል ተውኔት ያበቃል! 8
የሰው ሳይሆን የስርዓት ለውጥ 9
ነፃነት ለኢትዮጵያ 9
ኑሮ ውድነት በኢትዮጵያ 9
በኢትዮጵያ የጨለማው ዘመን ያብቃ 9
ልብ እንበል! 10
ወያኔ በሴቶች ላይ......... 10
አምባገነኑ የወያኔ መንግስት 10
ወያኔን የማስወገድ ትግላችን ተጠናክሮ ይቀጥላል!!! 11
የመሬት ወረራው አደጋ 11
ፈጣኑ ሎተሪ ሲፋቅ ያው ነው 11
በህዝብ ላይ የሚደርሰው መረን የለቀቀ ጭቆና እስከ መቼ? 11
የደም ውርስ 11
የወያኔ ስራዎች 12
ድህረ-መለስ አፈና በኢትዮጵያ 12
የዜግነት ግዴታችንን በጋራ እንወጣ 12
አቶ በረከት ስምዖን ምን ነካቸው ??? 13
የፖለቲካ ፓርቲዎችና የመንግስት መዋቅሮች በኢትዮጵያ 13
በኢትዮጵያ ፍትሐዊ የሃብት ክፍፍል እንዳይኖር የተደቀነው እንቅፋት!!! 14

Woyane is still cheating the world! 16

**Enough is enough:** 16

Amnesty International`s Statement 17
Punishment law 19
**Who Inherited Ethiopia?** 19
**Dictator Regime** 20

**Human Right in Ethiopia** 20
**Speech** 21

**Political situation in Ethiopia** 22

ወያኔ በቅዠት 23
አምላኬ ሰው ስራ! 23
ግፈኛው ወያኔ 23
ስፖርት 24

# About Tila

Realizing the fact that the digital age has empowered and made ordinary people across the world irrepressible beyond their imagination, **WE** aims to serve as a credible platform that will spread uncensored interviews, news, commentaries and analyses that are unlikely to see daylight in Ethiopia.

Fortunately, here is where you find **TILA**, the un-disputably best source of information serving the Ethiopian Diaspora community in Europe & America with a proven record of excellence in journalism.

TILA is a political magazine published and distributed by patriotic Ethiopians around Hessen region in Germany. Tila appears in Amharic, English and Germany Languages every 3 months. It is a magazine of quality, responsibility and standard. Entertainment and sport are among our coverage issues next to Ethiopian politics.

As a reader, you are to get useful political and current news in **TILA** than any other publication can offer you. More comprehensive analysis and interpretations than any other media can present to you. In fact, these are some of the qualities of **TILA** that has made it the largest circulating magazine in its category. **TILA** magazine has also partnered with ethiomedia.com, ethiogermany.de, ethiopiazare.com and afroaddis.wordpress.com among others, to deliver reliable and high quality content to our visitors.

Don't take the chance of missing this spectacular political magazine. Subscribe to it today! We promise, you won't regret your decision. Reach us on tilamagazine@yahoo.de & tilamagazine.yolasite.com

**Tila Magazine is yours Magazine!**

## ውድ አንባብያን

**ጥላ** መፅሄት በየሶስት ወሩ የሚታተም የፖለቲካ መፅሄት ነው።መፅሄቱ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መሰረት አድርጎ በጀርመን አገር የሚታተም ቢሆንም መረጃ መረቦችን በመጠቀም መላውን ዓለም የማዳረስ ዓላማን አንግቦ እየተንቀሳቀሰ ነው።

የአገራችንን ወቅታዊ ሁኔታና ጠቃሚ መረጃዎችን በማካተት ዝናን ያተረፈው የጥምረት መፅሄት አዘጋጆች ያቋቋሙት ጥላ መፅሄት የስሙ ስያሜ እንደሚያመለክተው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች በተበታተነ ሁኔታ የሚያካሂዱትን የትግል ሂደት በማስቀረት በአንድ ጥላ ስር እንዲሰባሰቡ ለማሳሰብና አቅጣጫ ለመጠቆም ነው።

የፖለቲካ ሃይሎች በተበታተነ ትግላቸው ጋት እንኳን መራመድ እንደማይችሉ በመገንዘብ የጋራ ትግል እንዲያካሂዱ ለማበረታታትም ጭምር ነው እ.ኤ.አ ከጥር 2012 ጀምሮ በዚህ ስም መፅሄቱ እንዲጠራ የወሰንነው።በመፅሄቱ አዝናኝና አስተማሪ ዝግጅቶች የሚካተቱበት ሲሆን ስፖርትም ትኩረት ያገኛል። **ጥላ** መፅሄት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሃሳቡን ያለምንም ገደብ በነፃነት የሚያቀርብበት ክፍት መድረክ በመሆኑ በመፅሄቱ የሚወጡት ፅሁፎች በሙሉ የፀሃፊዎቹን እንጂ የጥላ መፅሄት ዝግጅት ክፍልን የማይመለከቱ መሆናቸውንም መግለፅ እንወዳለን።

**ጥላ መፅሄት የእናንተው መፅሄት ናት!**



# EDITORIAL



## Regime change

**Songwriters:** NOAH, BRADLEY MICHAEL / YOUNG, KEVIN DUANE / BARRETT, TIMOTHY DWAYNE / FIFE, JOEY SETH / WYRICK, TRAVIS

Build it up, tear it down
My finger in the strings connected to your hands
I dance the mockery, a theme of decadence
Love, Life
Now I am sinking in this violence
This time emancipation is my right

This is what I want
For you to die
This is what I want
To be alive

Scene of complacency, an apathetic mind
But when it's brought to light, I see a king on a borrowed throne
Right now the violence taking over
This time regimes are changing in my mind
[ Lyrics from: http://www.lyricsmode.com/lyrics/d/disciple/regime_change.html ]
This is what I want
For you to die
This is what I want
To be alive

I'm so sorry my old friend
I'm leaving you tonight
So caught in this moment
The last breath of your life
**So Sorry**
This is what I want
(I am sinking in this violence)
For you to die
(emancipation is my right)
This is what I want
(the violence taking over)
To be alive
(regimes are changing in my mind)

So Sorry
Try To Understand(3X)

**``TILA Magazine is yours Magazine!**
**TILA is a Multi-lingual Magazine not only you read it, but also you will write on it!**



# ርዕሰ አንቀፅ



## የስርዓት ለውጥ

አስር የሚሆኑት ታዋቂ አቀንቃኞች የስርዓት ለውጥን አስመልክተው ያዜሙትን ዜማ ግጥም በርዕሰ-አንቀፅ የተጠቀምንበት ያለምክንያት አይደለም።ዜማው ለእኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ ወቅታዊ በመሆኑ ጭምርም እንጂ።አቀንቃኞቹ በዜማቸው አምባገነን ስርዓቶች መለወጥ እንዳለባቸው በግልፅ ቋንቋ ነው የሚናገሩት።በእርግጥ እነሱ ያ አይነት ችግር ያለባቸው አገሮች ዜጎች ባይሆኑም መዚቃ የዓለም ቋንቋ ናትና በችግሩ ለምንነደው ወገኖች አጋርነታቸውን በ4 ደቂቃ ዜማ ነው የገለፁበት።

በግጥሙ እንደተጠቆመው ተስፋ ፍቅርና ህይወት ምስቅልቅላቸው እንዲጠፋ በፈረዱ የአምባገነን አመራሮች ላይ "ሆ "ብሎ መነሳት ለነገ የማይባል መሆኑን አመላክተዋል።ህዝባዊ አመፅ ለእንዲህ አይነት ስርዓቶች ለነገ የማይባል መፍትሄ እንደሆነም እንቅጩን ይናገራል ዜማው። በግጥሙ የመጀመሪያ ዘውግ ላይ በግልፅ እንደተጠቆመው ለተነፈጉን መብቶች መከበር ማንኛውንም እንቅስቃሴ ማድረግ መብት መሆኑንና ሁሉም የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዲያደርግ ይመከራል።

እኔ(ህዝቡ) እንድ(ዲ)ኖር ባንፃሩ አንተ(አምባገነኑ)እንድትሞት (ከስልጣንህ እንድትገረሰስ) ነው የምፈልገው ይላል ቀጣዩ የግጥሙ ዘውግ።የግጥሙ ሶስተኛ ዘውግ ደግሞ እርግጥ ነው አምባገነኖቹ አየሩን አስፈሪ በማድረግ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ምን አገባኝ አይነት ስሜት ሊያሳድሩብህ ቢሞክሩም ጉዳዩን ወደ ብርሃን ከወሰድከው ንጉስህ የሌላ ዘውድ ተውሶ እንደሚያስተዳድርህ ቁልጭ ብሎ ይታይሃል።




ስለዚህ አዕምሮህን መብትህን ለማስከበር የስርዓት ለውጥ እንደሚያስፈልግህ አሳምነውና ጎራውን ተቀላቀል ነው ጠቅለል ያለው መልዕክቱ።

በተከታታይ ያሉትን ስንኞች ስንዳስስም የድሮው ጓደኛዬ*ስርዓቱን ማለቱ ነው* ዛሬ ማምሻውን እለይሃለሁ ስለዚህ አሁን ያለህ ቀሪ ነገር የመጨረሻ ትንፋሽህ ብቻ ነው ይለዋል።በጣም አዝናለሁ በአመፁ ውስጥ ሰጥሜያለሁ የተነፈግኳቸውን መብቶች ማስከበር መብቴ ነው።በእኔ አዕምሮ ስርዓቱ በመለወጥ ላይ ነው። እኔ(ህዝቡ) እንድ(ዲ) ኖር ባንፃሩ አንተ(አምባገነኑ)እንድትሞት (ከስልጣንህ እንድትገረሰስ) ነው የምፈልገው በማለት መደምደሚያውን በጣም አዝናለሁ እንድትረዳኝ እፈልጋለሁ እያለ ደጋግሞ በማሳሰብ ይቋጫል።የግለሰቦች ሳይሆን የስርዓት ለውጥ ነው የሚያስፈልገን!!!ጥላ መፅሄት እንደተለመደው አዳዲስ ፊቶችንና ሃሳቦችን ዕድሎችንና ልዩ የክብር እንግዶችን ይዛ ባላችሁበት ደርሳለች።መልካም ንባብ።ተሳትፎአችሁ አይለየን የእኛ መልዕክት ነው!

**ጥላ መፅሄት የእናንተው መፅሄት ናት! "ጥላ የሚያነቧት ብቻ ሳትሆን የሚፅፉባትም መፅሄት ናት"**




INFRASTRUCTURE

# ሰው ጥራ ቢሉት እራሱ መጣ

**Kidane Gebregziabher Lema/ Germany**

ለዘመናት አንባገነኖችን ስትቀበልና ስትሸኝ የኖረችው ሀገራችን ኢትዮጵያ እነሆ ህዝቧ ከድህነትና ከስደት አልወጣም;; ዛሬም እንደወትሮው የአንባገነኑን የመለስ ዜናዊን ራእይና ፖሊሲ ሳይበረዝና ሳይከለስ ማለትም ያንባገነኖችን አላማና ግብ ለማስፈፀም የራሱ ራእይ የሌለው በተራው በወንበሩ ጉብ ብሏል;;

አንድ ነገር ግልፅ ለማድረግ የመለስ ፖሊሲና ራእይ ምንድን ነበር ? ለህዝቡስ ምንድን ነው የጠቀመው?ሰባ ፐርሰንቱ በከፍተኛ ድህነት ጣራ ሲኖር ከአስር እስከ አስራ አምስት ፐርሰንቱ ደግሞ በስደትና በስር
ቤት ይማቅቃል፤እንግዲህ የቀሩት እነሱና ከነሱ ባላማ የተመሳሰሉ ሆዳሞች ይሆናሉ ማለት ነው።

ታዲያ ይህም ሆኖ ባምባገነኑ የወያኔ ስርአት አፈናው፤ ሙብት ረገጣው፤ሙስናውና የፍትህ እጦቱን ነው ራእይና ፖሊሲ መለስ ሀያ ሁለተኛ አመት ይቀጥላል ብሎ የሚለን ፤ ይህ አይቀጥልም ልንል ይገባል። ያንባገነኖች ዱላ ቅብብሎሽ ማቆሚያ ሊበጅለት ግድ ነው። በነፃነት ለመኖር ነፃነት ብለን መውጣት አለብን፤ ለነፃነት መሞት ለኛም ለምንተካቸውም ልጆቻችን ህያው መሰረት ዘላለማዊም ክብር ነው።

ይህ ካልሆነ ግን ነፃነታችንንም እንደተገፈፍን ልጆቻችንንም ላምባገነኖች ባርያ አድርገናቸው የማይቀረውን ሞት ያለክብር
እንሞተዋለን። ስለዚህ ሁላችንም ይህንን ስርአት ከስሩ ገርስሰን ለመጣል ነፃነትና ሙብትን ለማስከበር ከሚታገሉ ወገኖች ጋር መተባበር፤ ፍትህ፤ ነፃነትና እኩልነት የሰፈነባት ሀገር ለመገንባት መነሳት ይጠበቅብናል።

# ጨካኙ የወያኔ መንግስት

**Abel Assefa/Hof**

አምባገነኑ የወያኔ መንግስት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ቀላል የማይባል ግፍ እና በደል ሲፈጽም ለ20 አመታት ዘልቋል።የቀድሞ አምባገነናዊ መንግስት ተገርስሶበምትኩ የወያኔ መንግስት ቢተካም ከቀድሞ የአምባገነንነት አገዛዝ የበለጠ ጨካኝ እና ለህዝብ የማይራራ የጥቅም እና የራስ ወዳድነት እንዲሁም ወገንተኛ የሆነ አረመኔ መንግስት ነው።የወያኔ መንግስት ማለት የህዝብ ችግር መራብ እንዲሁም ስቃይ የማይረዳ ህዝቡ በአቅሙ ያፈራውን ንብረት እየቀማ የገበሬውንም መሬት በመንጠቅ የግል ጥቅማቸውን ለሚያሳድዱት ለኢህአዴግ አባሎች እየሰጥ ምስኪኑን የኢትዮጵያን ህዝብ እንዲቆረቁዝ እያደረገ ቆይቶ በማድረግ ላይም ነው።

ህዝቡን በማይፈልገው ፓርቲ ማለትም ኢህአዴግን እንዲመርጡ በግዳጅ እና በአፈሙዝ እያስፈራራ በግድ ምረጡ በማለት በህይቡ ላይ በጭካኔ አምባገነንነቱን በማሳየት ለ20 አመታት ሲረግጥ ሲገዛ ቆይቷል።አሁንም ለ21ኛ ለመራራ እና ለስቃይ ጊዜ ደርሰናል።የወያኔ መንግስት ህይቡን በብሄር እየከፋፈለ በሰላም እና በፍቅር በመከባበር የሮነውን ህዝብ እርስ በእርስ እንዲጋጭ እንዳይስማማ እንዲሁም ህዝቡ አንድ ሆኖ ለነጻነቱ እንዳይታገል ፍትህ እና ዴሞክራሲ የሰፈነበትስ መንግስት እንዳይመርጥ በጉልበቱ ትጠቅሞ በደል እያደረሰ ይገኛል።

ይህ ወያኔ የሸሙት አምባገነኑ መንግስት ዛሬ ስትራቴጂ በመጠቀም ላይ ይገኛል እና እኛ የኢትዮጵያ ህዝብ በአንድነት ይህን የግፍ አገዛዝ ላይ የተመረኮዘውን የወያኔ መንግስት ለመደምሰስ ቆርጠን ተነስተናል።በህዝባችን ላይ እየተሰራ ያለውን የግፍ አገዛዝ ለመደምሰስ ተነስተናል።ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ ፍትህ ዴሞክራሲ የሰፈነበትን ህዝቡ በአንድነት በእኩልነት በፍቅር በመከባበር እንዲኖር ያለንን ሃይል ተጠቅመን ከዚህ ከወያኔ አምባገነን ስርዓት ለመውጣት እንታገላለን።ድል ሰላም ዴሞክራሲ ለጠማው ለኢትዮጵያ ህዝብ ያለንን ሃይል እንሰጣለን።ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

# ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም

**Mesfin Beyene/Hof**

ሃገር ማለት የልዕልና የክብር ምልክት መገለጫ እንጂ የስደትና የመከራ ቀንበር አይደለም።ብዙ አምባገነን መሪዎች በዓለማችን በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ቦታዎች ነበሩ።እነዚህ አምባገነን መሪዎች ታዲያ እንመራሃለን የሚሉትን ህዝብ ላይ የተለያዩ ግፎች ሲፈጽሙ ታይተዋል።እነዚህ ግለሰቦች በፈጸሙት ግፍ ብዙ ህጻናት ያለወላጅ ቀርተዋል፤ብዙ አዛውንት ያለጧሪ ቀርተዋል፤አብዛኛው ህዝብ ያለንብረት ቀርቷል፤ አብዛኛውን ህዝብ አስረዋል፤ አብዛኛውን ህዝብ ገድለዋል።እንደዚህ አይነት በደል ካደረሱ መሪዎች አንዱ በቅርብ በሞት የተለዩት የወያኔው ሊቀመንበር መለስ ዜናዊ ናቸው። በአሁኑ ሰዓት ስልጣን ላይ ያሉት የወያኔ ባለስልጣናት ሃገራችንን ወደባሰ ውድቀት ከመውሰድ በስተቀር የኢኮኖሚም ሆነ የፖለቲካ መሻሻል (ዴሞክራሲ) የሚያመጡ ሳይሆን የባሰ ውድቀት የሚያመጡ ናቸው። እናም ሁላችንም ሃገራችንን ከዚህ የወያኔ አምባገነኖች ነጻ እናውጣ!!!

# በጋራ እንታገል

**Doriyan Kassahun Fanta/Hof**

ጠላታችን አንድ ነው፤ችግራችን ተመሳሳይ ነው፤ የምንኖረው አንድ ሃገር ውስጥ ነው፤አንዳንዶቻችን የቆምነው ለራሳችን ብሄር ነጻነት ነው፤አንዳንዶቻችን ደግሞ ትግላችንን ህብረ-ብሄር ነው አንድ ብሄረሰብ የሚኖረው በሌላው ብሄረሰብ ውስጥ ነውና።ስለዚህ የግል ጉዟችንን ትተን አንድ እንሁንና ሁላችንም ከወያኔ ዘረኝነት እርግጫ ነጻ እንውጣ።ዛሬ እኛ ኢትዮጵያውያን መተንፈስና መታገል አንድ የሆኑበት ጊዜ ላይ ደርሰናል።ከሁለት አንዱን ያቆምን ዕለት ደግሞ መሞታችን አይቀርም።
ይህ ትውልድ አገራችንን ይስጨነቃትን አስቀያሚ ሥርዓት አስወግዶ አዲሲቷን ኢትዮጵያ ግንባታ የሚጀምር ትውልድ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ይዞት የሚነሳው መንፈሳዊ አላማ የአገሪቱን አላማ አስጠብቆ ከዴሞክራሲያዊ የስልጣን ሽግግር የምትደርስበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ሁሉንም የፖለቲካ ሃይሎች ያካተተን የሽግግር መድረክ ያለመ ስለሆነና ወደዚያው መድረክ ድልድዩም ሃገራዊ አንድነትና ዴሞክራሲን የሚሹ ሃይሎችን ሁሉ በጋራ ያስተባበረ ትግልን የሚያጧጡፍ በመሆኑ ከግባችን ለመድረስ ከህብረት ትግል ውጭ የሚቻል አይደለም።

ወያኔ እንዳለፉት መንግስታት ሁሉ በጠመንጃ ስለዴሞክራሲ ሲለፍ የነበረውን ቡድን በአንድ ራስ ሁለት ምላስ እንዲሉ ሆነና ብዙም ሳይቆይ በጡንቻ የመመካት ጭፍን የድቅድቅ ጨለማ ጉዞ ሙጥኝ በማለት የንጹሃንን ደም በግፍ ማፍሰስ የተለመደ መገለጫው ሆኗል።

# የታሪክ ተጠያቂዎች አንሁን!

Getachew Eguale Gebremedhen/ Germany

ከ Juni 19, 2012 ወዲህ የኢትዮጵያን ህዝብ በሙሉ ሲያነጋግር የቆየው የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ መኖር አለመኖር በይፋ ለአለም ህዝብ ከዚህ ዓለም ማረፋቸው የፈጣሪ ስራ እንጂ የሰው ስራ አይደለም ብለን መቀበል የሰብዓዊነት መለኪያችን ነው።

አስደናቂ የሆነው በተከታታይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አለቃ የነበሩት በመለስ የተሾሙት አባ ጳውሎስ መሞታቸው በመለስ ጥብቅ በሽታ ዙሪያ ኢትዮጵያ የምትመራው በህገ-መንግስት በስርዓት እንጂ በአንድ ሰው አይደለም መለስ ዜናዊ ቢሞቱም ስርዓቱ ይቀጥላል ያሉት ጄነራል ሳሞራ የኑስ በጥብቅ ታመዋል መባሉ ወዘተ የተያያዙ መሆናቸው የኢትዮጵያን ህዝብ እያነጋገረ ነው።

ባጭሩ የአምባገነኑ መለስ ዜናዊ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት የስርዓት ለውጥ የማያመጣ በመሆኑ ህዝባችን ሆይ በአንድነት ለአጠቃላይ የስርዓት ለውጥ የጋራ ትግል እንድናደርግ ጥሪዬን አቀርብልሃለሁ።

# ለውጥ የለም እንጂ ......

Hilina Dawit/ Nürnberg

የአቶ መለስን መሞት ተከትሎ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የሰብዓዊ መብት ረገጣ እየተባባሰ መጥቷል ለምሳሌ ያህል በአቶ መለስ ሞት ጊዜ አላለቀሳችሁም ተብለው እስር ቤት ብዙ ወጣቶች ተወርውረዋል።ሌላውን የመብትና የሰብዓዊ መብት ረገጣ ትተን ማለት ነው።

አቶ መለስ ሞተ እንጂ ስርአቱ ምንም አይነት ለውጥ አላመጣም ለምን ቢባል ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም ነውና።አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ በሃሳባቸው የሚመሩ ሳይሆን የአቶ መለስን ስትራቴጂ ለመፈፀም የተቀመጡ ናቸው።አራት ነጥብ።

ለአገራችን ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ስር ነቀል የሆነ ለውጥ ብቻ ነው።ለምሳሌ:- በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ የማይገባ፤በዘረኝነት ያልተበረዘ ፤በህግ የበላይነት የሚያምን፤የህዝብን ድምፅ የሚያከብር፤ ሰብአዊ መብቶችን የሚያስከብር፤ ወዘተ...በጥቂቱ እነዚህን ለውጦች በኢትዮጵያ ውስጥ ነፍስ የሚዘራ መንግስት ብቻ ነው የሚያስፈልጋት ኢትዮጵያችን።የጉልቻ ለውጥ ሳይሆን ወይም መለስን በሃይለማርያም መተካት ሳይሆን ስር ነቀል ለውጥ ብቻ ነው አገሪቱን ወደ ዕድገት ጎዳና የሚወስዳት።ስለዚህ በመለስ ሞት ሳንዘናጋ ለስር ነቀል ለውጥ የጀመርነውን ትግል አጠናክረን እንቀጥል! ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!

# ህፀፀ ወያኔ!

Tigist Belay Demissie/ Pfarrkirchen

- የወያኔ መንግስት አግባብ ያልሆነ አመራር የፈጠረው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ለብዙሃን ወገኖች ህይወት መጥፋትና ወደተለያዩ አገራት ለስደት መዳረግ ምክንያት ሆኗል።
- የወያኔ ተለጣፊ ድርጅቶች አፋቸውን ተለጉመው ዝንባቸውን እሽ እያሉ ጌቶቻቸው የሚወስኑላቸውን ከዳር ቆመው ይጠባበቃሉ አዕምሮአቸው የነጠፈ በመሆኑ ከነሱ ጭንቅላት የሚወጣ ቁምነገር የለም።አሁንም ያው ናቸው።ለሆዳቸው እንጂ ለህሊናቸው ማደር ካቆሙ 21 ዓመታት ተቆጠሩ።አሁንም አልተማሩም አይማሩም መማርም አይፈልጉም ነገር ግን የተማረውን ህዝብ ያተራምሳሉ እርስ በርሱ እንዳይግባባ እሳት ይለኩሳሉ አንዱን ካንዱ ያናክሳሉ።የወያኔ ባለስልጣናት ጊዜ ለመግዣ የሚያደርጉትን አጉል ውዥንብር ትተው ለመጀመሪያ ጊዜ ለህዝብ አስረክበው የሰላም እንቅልፍ ቢያንቀላፉ ይመረጣል።
- የወያኔ የውስጥ ለውስጥ ሽኩቻ ለለውጥ ሳይሆን ከምንም በላይ ለሰላም መናጋት ለደም መፋሰስና ለህልፈተ ህይወት መዳረግ ዋና መሰረት ከመሆኑ ውጪ ሌላ ትርጉም የለውም።
- ይህ አምባገነን ስርዓት በዘር በጎሳ በሃይማኖት አገሪቷን እየከፋፈለ ወደማያባራ የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ከመክተቱ በፊት አደብ የሚገዛበትን ስልት የመንደፍና ለተግባራዊነቱም መታገል ግድ ይለናል።ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!

# በጋራ ተሳትፏችን የወያኔ የይምሰል ተውኔት ያበቃል!

Yohanes Samson/Bad - Hersfeld

አምባገነንነታቸዉን በእጅጉ ካጠናከሩ መንግስታት መካከል በኢትዩጵያ የተንሰራፉት ወያኔዎች ግንባር ቀደም ናቸው።ስልጣን ከያዙ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የፈፀሙት በደል በእጅጉ ከፍተኛ ነው።

በሰሜን አፍሪካ የታየው የነፃነት አብዮት እንቅልፍ የነሳቸው ወያኔና ግብረ-አበሮቹ በከፍተኛ በጀት ሰላዮችን በብዛት በትነው የህዝቡን የዕለት ኑሮ እያወኩ ነው።በመላው አገሪቱ ብዛት ያላቸው ሰዎች እየታሰሩና እየተገደሉ ነው።በየእስር ቤቱ የታጎሩትም በዘግናኝ ሁኔታ እየተሰቃዩ ነው።ከህግ ውጪ ይገደላሉ።በእስር ላይ እንዳሉ ተሰቅለው ይገረፋሉ።በዘር ፍሬያቸው ላይ ጉዳት ይደርሳል።በኤችአይቪ በተበከለ መርፌ ሆን ተብሎ ይወጋሉ በሚል ዓለምአቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሚጋቾች አቤት እያሉ ነው።

በአሁኑ ሰዓት 24 ከፍተኛ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አመራሮችና ጋዜጠኞች በአሸባሪነት ተፈርጀው እስር ቤት ናቸው።በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ ግለሰቦችም ሁኔታ በአገሪቱ እስር ቤቶች ተወርውረው እየተሰቃዩ ይገኛሉ።አለም አቀፍ ጫናው ካልተጠናከረ የሞት ወይም የዕድሜ ልክ እስራት ይጠብቃቸዋል።

አሸባሪ ከተባሉት መካከል የመድረክ አመራር አባል አቶ አንዷለም አራጌ፣ነፃነት፣መኮንን፣ጋዜጠኞቹ እስክንድር ነጋና ርዕዮት አለሙ ይገኙበታል።ነፃነት ለ23 ቀናት በተከታታይ መገረፉን ውሃ ውስጥ እየተዘፈቀ መቀጣቱና ልብሱ ተወስዶ ራቁቱን እንቅልፍ ተከልክሎ መቆየቱን ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ ተናግሯል።

ሂዩማንራይት ዋች(Human Rights Watch) እና አምንስቲ ኢንተርናሽናል (Amnesty International) ባለፈው ወር ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ ህግን እያጣመሙ ሰዎችን እያሳደዱ በመቅጣት ረገድ ኢትዮጵያ እጅጉን የምታሳስብ አገር ሆናለች።በዓለም ላይ የዚህ ዓይነት ተግባር በመፈፀም ኢትዮጵያ ብቸኛዋ አገር ሆና

አግኝተናታል ሲሉ ወቅሰዋል።የአገሪቱ አምባገነንነት መከፋት ባስከተለባቸው ከፍተኛ ስጋት የጋራ መግለጫ ለማውጣት እንዳስገደዳቸው አስታውቀዋል።በደቡብ ክልል የሁለተኛ ደረጃ መምህር የኔሰው ገብሬ ያለፍትህና ነፃነት ከመኖር መሞት ይሻላል በማለት በክልሉና በመላው አገሪቱ የሚፈፀመውን የአምባገነኖች ግፍ በመቃወም በቅርቡ በአደባባይ ራሱን በማቃጠል ተቃውሞውን ገልጿል።ህዝቡም በምሳሌነት እንዲከተለው ጠይቋል።

ዛሬ ኢህአዴግ የሞት ጥላ ከመራቅ ይልቅ እየጎላ በእያንዳንዱ ቤተሰብ በር ላይ ቆሞ እያንኳኳ ነው።ቀድሞ ካልተመታ አደጋው የከፋ ነው።ራሳችንንና ወገናችንን የማዳን ሃላፊነት ስላለብን ተቃውሞና ትግላችንን አጠናክረን የሞት ጥላውን እናስወግድ።

# የሰው ሳይሆን የስርዓት ለውጥ

**Hanna Nigusse/Meseret Kebede - ARNSBERG**

በኢትዮጵያችን የስርዓት ለውጥ ለማምጣት መላው ህዝብ በሚታገልበት በአሁኑ ወቅት በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ሞት ምክንያት የተሻለ ለውጥ ይመጣል የሚል ተስፋ ቢያድርብንም ያሰብነው እንደማይሆን አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር እቅጩን ነግረውናል።ስለዚህ የግለሰቦች ጉልቻ መለዋወጥ ወጡንም አገሪቱንም ስለማያጣፍጥ ትግላችን ተጠናክሮ መቀጠሉ ግድ ሆኗል።በመሆኑም ዛሬም እንደ ትናንቱ ትግላችንን ማፋፋም ከሁላችንም ይጠበቃል።

በአገራችን ሁሉን አቀፍ ለውጥ ለማምጣት ደግሞ አሁንም የሰፊውን ህዝብ ድጋፍ ይፈልጋልና ለጋራ ትግል በጋራ ለመሰለፍ አሁንም ቃላችንን ማደስ አለብን።

ስለዚህ አሁንም እንደ ቀድሞው እጅ ለእጅ ተያይዘን አገራችንን ሌሎች ከደረሱበት የሰላምና የዴሞክራሲ ደረጃ ለማድረስ የኔ ድርሻ ምን ያደርጋል ሳንል የበኩላችንን ጥረት ማድረግ ይገባናል።ጋን በጠጠር ይደገፋል እንዲሉ አበው የምንችለውን በማድረግ ሃላፊነታችንን እንድንወጣም የዘወትር ጥሪዬ ነው።እግዚያብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ!

# ነፃነት ለኢትዮጵያ

**Dina Yosef/Klümba**

በአሁኑ ሰዓት የወያኔ አገዛዝ የህዝባችንን ነጻነት በማሳጣት ወግና ባህሉን እንዲሁም አንድነቱን ጠብቆ የኖረውን ውድ ኢትዮጵያዊ ወገን በዘርና በሃይማኖት በመከፋፋል አንድነቱን አሳጥቶታል። እንዲሁም በዴሞክራሲ ስም እጅግ ብዙ የማጭበርበሪያ ስልቶችን እነሆ በሰፊው በማራመድ ላይ ይገኛል።ይህም አልበቃ ብሎ ብዙሃኑን ለስደትና ለሞት አጋልጧል።ለመንገላታትም ዳርጎታል።

ለዚህም ሲባል እኛም ከሞት የተረፍን ስደተኞች ለስደት የዳረገነን ጨቋኙን ዘረኛውን አምባገነን መንግስት በተወለድንበትና ባደግንበት አገር እንደባይተዋር ነፃነቱን አጥቶ በሀገር እንዳይኖር ጭቆናን ጠልቶ ሃገሩና ወገኑን ትቶ በስደት ላይ ነፃነትን ፍለጋ እየተሰደደ ያለውን ወገናችንን ልንታደገው የምንችለው እንደገናም በወያኔ ያጣነውን ነፃነታችንን የምናገኝበት መንገድ ሊገኝ የሚችለው በአገር ብቻ ሳይሆን በአህጉር ደረጃ አሸባሪ የሆነውን የወያኔ ዘረኛ መንግስት በአንነት ሆነን መታገል ስንችል ብቻ ነው።

በመጨረሻም መልዕክቴ በአንገብጋቢነት ሊሆን የሚችለው ነፃነት የጠማውን ተጨቁኖ ያለውን ህዝባችንን በተለይም አገሩን፤ቤተሰቡን ጥሎ ያለው ..........እንዲሁም እኛ በስደት ላይ ያለነው ወገኖች በሞላ ይህ አምባገነን የወያኔ አገዛዝ ከስልጣኑ የሚነሳበትን መንገድ መፈለግ ብቻ ነው። ነፃነት ለኢትዮጵያ!!!

ምንም እንኳን በገዢው ፓርቲ አማካኝነት ተወዳዳሪ የሌለውና በስልት የሚያካሂደው አፈና ቢኖርም ታሪክ በተደጋጋሚ የመሰከረው ነገር ቢኖር አፈና ለዘላለም ሊቀጥል እንደማይችል ነው።እኛም ሴቶች ይህን ግፍና በደል ለመታገል ከወንድሞቻችን ጎን እንዲሁም የኢትዮጵያን ነፃነት ዴሞክራሲ ከሚፈልግ ጋር ጎን ለጎን አብረን በመቆም አጥብቀን ልንታገለው ይገባል።የሴቶች መብት ይከበር!!!

# ኑሮ ውድነት በኢትዮጵያ

**Hanna Abebe/Zeil**

አምባገነኑ የወያኔ መንግስት በኢትዮጵያ አገራችንና በወገኖቻችን ላይ እያደረሰ ያለው ግፍ ፣መከራ ስቃይና በደል ከዚህ በፊት ከነበሩት መንግስታት ጋር ሲነፃፀር መቶ ፐርሰንት የከፋና ከፍተኛ ሰብአዊና ቁሳዊ ኪሳራ የደረሰበት ሆኖ እናገኘዋለን።

መቼም በኢትዮጵያ ያለው የኑሮ




መወደድ ኢህአዴግ መላው አገሪቱን ከተቆጣጠረበት ማግስት አንስቶ የተባባሰ በመሆኑ የሚከተለውን የኢኮኖሚ አቀጣጫ ችግር አጉልቶ አሳይቷል።ገዥው መንግስት በተደጋጋሚ ፖሊሲውን እንዲያስተካክል የተሰጠውን የምሁራን አስተያየት ውድቅ በማድረግ የራሱን ስልጣን በማራዘም ላይ ብቻ ተጠምዶ ይገኛል።በዚህም መሰረት አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ከተረጂነት የተላቀቀ ሳይሆን ለረሃብና ለችግር በመዳረግ ላይ ነው።

ስለሆነም በአገራችን ላይ የተጋረጠውን ኢህአዴግ ሰራሽ ችግር ለማስወገድ አገሬ ናት የምንል ዜጎች ሁሉ በአገር ማዳን ትግሉ ውስጥ እንድትሳተፉ ታሪካዊ የትውልድ ሃላፊነት እንዳለብን አውቀን የበኩላችንን እንድንወጣ አደራ እላለሁ።

# በኢትዮጵያ የጨለማው ዘመን ያብቃ

**Dawit Tesfaye/Hadamar**

አንድ አምባገነን አልፎ በሌላ እየተተካ የመከራና የችግር ዘመን ሳያቋርጥ ህዝቡ ፍዳውን ሲያይ የኖረባት አገራችንን የሚገዛው የዘመናችን አገዛዝ በመለስ ዜናዊ

ቁንጮነት የጨለማ እድሜውን ከጀመረ ሃያ አንድ ዓመታት አለፈው።ይህ አምባገነን ቡድን ወደ ስልጣን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ የመድብለ ፓርቲን ዴሞክራሲ አራምዳለሁ ሰብአዊ መብቶችን አስከብራለሁ ብሎ ቢመፃደቅም ይህ ሁሉ ከተፃፈበት ወረቀት በላይ የማያልፍ ለመሆኑ የአገዛዙ የ21 ዓመታት እኩይ ተግባራት ምስክሮች ናቸው።

የዛሬይቱ ኢትዮጵያችን በዴሞክራሲና በሰብዓዊ መብቶች መከበር ምትክ የመሰብሰብ የመፃፍ የመናገር ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ በአጠቃላይም ዜጎች ሃሳባቸውን በነፃነት የመግለጽና የመደራጀት መብቶቻቸውን የተነፈጉበትና የአንድ ፓርቲ አምባገነንነት የሰፈነባት የፍትህ አካላት የዜጎችን ደህንነት ከመጠበቅ ይልቅ የመጨቆኛና የማፈኛ መሳሪያ በሆኑበት ሁኔታ ላይ ትገኛለች።አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ይህ የግፍ አገዛዝ መቆም አለበት በሁሉ አቀፍ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መተካት አለበት ካለ ቆይቷል።አገራችን በዚህ አስከፊ ሁኔታ ከቀጠለች ለግዛታዊ አንድነቷና ለህዝቧ ሰላም አብሮ መኖር ዘላቂና ፍትሃዊ እድገት ያሰጋታል።የኢትዮጵያ ህዝብ ይህ አይነት አምባገነንነት እንዲቀጥል አይፈልግም አይፈቅድምም የሚል እምነት አለኝ።

የህወሃት ኢህአዴግ አስከፊ አገዛዝ ቅንቅን እንደበላው ዛፍ በህዝብ ትግል እንደሚገረሰስ አያጠራጥርም።

ይህ መውደቂያው የተቃረበ አምባገነናዊ አገዛዝ ሌላው ቢቀር ለራሱ ሲል እንኳን የያዘውን አካሄድ መለወጥ እንዳለበት ሊገነዘብ ይገባዋል።የአምባገነኑ ቁንጮ አቶ መለስ ዜናዊ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው የተነሳ ቀጣይቱ ኢትዮጵያን ብሩህ ለማድረግ አሁን በስልጣን ላይ ላለው ፓርቲም ይሁን በጠቅላይ ሚኒስትርነት ለተተኩት ልዩ አጋጣሚ ነው።ይህ ለሁሉም ክፍሎች ሊጠቅም የሚችል ዕድል እንዳያመልጥ ያለው ጨቋኝና ከፋፋይ የሆነ የአገዛዝ ስርዓት ለመለወጥ ፈቃደኛና ቁርጠኛ መሆን አለባቸው እንላለን።ስለሆነም አገራችንን ከአደጋ ለማዳንና እውነተኛና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመመስረት የስልጣን ምንጭ የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ መሆኑ የሚረጋገጥበት ስርዓት እንዲፈጠር የሚያስችል ሂደት እንዲጀመር እጠይቃለሁ።

**ውድ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ!** በስምህ እየተነሱ የራሳቸውን የግፍ አገዛዝ የሚጭኑብህን እምቢ በላቸው!በአገርህ እንደ ዜጋና እንደ ሰው የሚገባህን መብትና ነፃነት የሚነፍጉህን እንደማትገዛ አሳውቃቸው!የጭቆና አገዛዝ መቆም አለበት ብለህ በአንድነት ተነስ።በሃይማኖትህና በቋንቋህ ሊከፋፍሉህና የግዛት ዘመናቸውን ሊያራዝሙ የሚፈልጉትን ሁሉ ይበቃኛል አትከፋፍሉኝ በላቸው!" አገር የጋራ ነው ሐይማኖት የግል ነው" የሚለውን ብሂል አትርሳ።ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

# ልብ እንበል!

**Zewdinesh Nigatu/Alsfeld**

አገራችን ዛሬ የሚያስፈልጋት ህዝብን እያስለቀሰና እያስመረረ በረሃብ እየቀጣ ታይቶ ለማይታወቅ ስደት እንግልት እስራት የዳረገውን አገዛዝ ከነግሳንግሱ ከአገራችን መሬት በማስወገድ በምትኩ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በማስፈን ለሁሉም እኩል የሆነች አንዲት ዴሞክራሲያዊት አገር እውን ማድረግ ነው።

ስለሆነም ዋነኛው ትግል አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ሊወገድ የሚችልበትን ስልት በመንደፍ በጋራ ትግልና ጥረት ህዝቡ የሚያደርገውን ትግል ሁሉም አካል ተደራጅቶ የአቅሙንና የችሎታውን አስተዋፅኦ በማድረግ በማጠናከርና ከመቼውም በበለጠ ለለውጥ ተግተን መስራት ይገባናል።ወያኔዎች ነጋ ጠባ ግራ የሚያጋባ ፕሮፓጋንዳቸውን እየለቀቁ ውሸቱን እውነት እያስመሰሉ ዕድሚያቸውን ለማራዘም ሲታገሉ ልንፈቅድላቸው አይገባም።

በወያኔ ስርዓት ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ተደረገ ተብሎ በራሳቸው ሚዲያ ሲገለፁ ከረሙ ለመሆኑ ማን ለማን በሰላም አሸጋገረ?ይህ የሚያሳየው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ቦታ በማን መያዝ እንዳለበት ያስጨነቃቸው መሆኑ ነው።የስልጣን ሽግሽግ በማድረግ የተለመደውን የአፈና ስርዓት ቀጥለውበታል።የወያኔ ስርዓት በምርጫ ሳጥን ይወገዳል ማለት ሞኝነት ነው።ምክንያቱም ከላይ እስከ ታች ምርጫ ቦርዱ በወያኔ ካድሬዎችና አባላት የተሞላ በመሆኑ ህዝቡ የፈለገውን እንዳይመርጥ ያደርገዋል።ወያኔ እራሱ ያፀደቀውን ህገ-መንግስት አያከብርም።

ስለሆነም በጠንካራ ክንዳችን አምባገነኑን ስርዓት በሃይል በህዝባዊ አመፅ ጭምር ከስሩ ገርስሰን በመጣል አገራችንን እንታደጋት።

# ወያኔ በሴቶች ላይ........

**Liya Yosef/Klümba**

ሴቶች እህቶቻችን ከፍትህ እጦትና ሰብዓዊ መብት አለመከበር የተነሳ ወደመካከለኛው ምስራቅ ወደ አረብ አገር በኮንትራት ሰራተኝነት እየተላኩም ይህ ነው የማይባል የአካልና የአዕምሮ ሰቆቃ ማለትም መደፈርን ኢ-ሰብዐዊ የሆኑ በደሎችና የአካል መደብደብን እንዲሁም ከዚህ ያለፉ በደሎችና ግፍ እየተፈጸመባቸውና ለሞት እየተዳረጉ ነው።

ሁሉም የኢትዮጵያ ዜጎች እንደሚከተሉት ሴቶችም በነፃነት የመደራጀት እንዲሁም በሃገሪቱ የፖለቲካም ሆነ የማህበራዊ ጉዳዮች በኢኮኖሚ ዘርፍ ዙሪያ ያላቸውን ሃሳብ በነጻነት መግለፅ እንዳይችሉ መብታቸውን ከማንም በላይ ተነፍገዋል።

የገዢው የወያኔ ቡድን ሃሳብን በነፃነት ሴቶች መግለፅ እንዳይችሉ የሚያደርገው አፈናና እስር ለብዙሃን ሴቶች የስቃይ፤የሰቆቃ ህይወት ተዳርጓል።በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ለፍትህና ለዴሞክራሲ ለፖለቲካ ለሰብዐዊ መብቶች የሚታገሉ ሴቶች ይዋረዳሉ።ለአሰቃቂ ሁኔታም ለእስርና ለስደት ይደረጋሉ።

# አምባገነኑ የወያኔ መንግስት

**Meron Berhane/Zeil**

ዘረኛና አምባገነኑ የወያኔ መንግስት ሀገራችንና ወገናችንን አሽማቆ መግዛት ከጀመረ ይኸው 21 ዓመት ሞላው።አገራችን ኢትዮጵያን በአሁኑ ወቅት ህዝቦች ከገቡበት የስቃይ ማጥ ውስጥ ለማውጣት ወያኔና በወያኔ ጉያ ስር ተሸጉጠው የህዝብን ሃብትና ንብረት በመዝረፍ የሚቃወማቸውን ህዝብ ለእስር ለሞትና ለእንግልት የሚዳርጉ ባለስልጣናትን ለማጋለጥ እኛ በስደት የምንገኝ ኢትዮጵያውያን በአንድነት ተባብረን ድምፃችንን ማሰማት ይገባናል።

ድምፃችንን ለዓለም መንግስታት በማሰማት እና በአገር ውስጥ የሚገኙ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንን በማስተባበርና በመደገፍ የወያኔ አገዛዝን በመገርሰስ የህዝቦችን እስር ስደትና ስቃይ ለማስቆም የጋራ ትግል ማድረግ አለብን!አምባገነኑን ስርአት ለማስወገድ ከሚታገሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጎን መሰለፍም ይገባናል!ድል ለህዝባዊ ትግላችን!!!

# ወያኔን የማስወገድ ትግላችን ተጠናክሮ ይቀጥላል!!!

**Emebet Setegn/Neuburg Donau**

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ 21 ዓመት ሙሉ ሲያደርግ እንደነበረው ሁሉ አሁንም በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን ግፍና ሰቆቃ አጠናክሮ ቀጥሏል።የወያኔ አመራሮች ሰውን በማሰቃየት የሚደሰቱ (**Sadist**) መሆናቸው ከኢትዮጵያ አልፎ በመላው ዓለም የታወቀ ጉዳይ ነው።

ኢህአዴጎች በረሃ ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ ከነሱ የተለየ አቋም የያዙ አልያም ወደፊት ይቃወሙን ይሆናል ብለው የጠረጠሩትን ወዳጆቻቸውን ሳይቀር አሰቃይተዋቸዋል ገድለዋቸዋልም።ነፃ ልናወጣ ተነስተናል ያሉት ህዝብ በረሃብ ሲገረፍ ለእርዳታ እህል መግዣ በተመፀወተው ተምነሽንሽዋል።ከበረሃም ወጥተው መላው የኢትዮጵያን ከተሞችና ገጠሮች በማጭበርበርም በጉልበት ከተቆጣጠሩ በሁዋላ መሰሪ ስራዎቻቸውን የሚቃወሙ ሰዎችን ማሳደድ ማዋከብና ማሰቃየት የዘወትር ተግባራቸው ሆኗል።

በአሁኑ ሰዓትም ስለሃገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ በግልፅ የሚዘግቡ ጋዜጠኞችን እንዲሁም በሙስሊም እምነት ተከታዮች ላይ እያካሄደ ያለው የጭፍጨፋ ዘመቻ ብሎም በዋልድባ ገዳም ያሉትን መነኮሳት ሳይቀር ማፈናቀሉና ማሰሩን አጠናክሮ ቀጥሎበታል።

ስለዚህ ይህ አጥፊ ቡድን አሁንም በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን የጥፋት ዘመቻ ባለማቆሙና ወደ ሰላማዊ መድረክ የመምጣት ፍላጎትም ሆነ የሞራል ብቃት ስለሌለው በግድ በሃይል ግጠሙኝ ያለ አምባገነን ገዥና ሽብርተኛ መንግስት በመሆኑ አገርና ትውልድ ከመጥፋቱ በፊት የተፈጠረልንን ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም መለስ ዜናዊ የገነባቸውን የአምባገነንና ዘረኛ አገዛዝ መላ ኢትዮጵያውያን ተባብረን ይህን የሻገተ ስርዓት ለመገርሰስ ዛሬውኑ እንነሳ! ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

# የመሬት ወረራው አደጋ

**Yohannes Selamu Benti/Hof**

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና በአብዛኛው በለጋሽ ሀገራት እርዳታ ላይ የተንጠለጠለ ሲሆን የወያኔ መንግስት እየተከተለ ባለው የመሬት ፖሊሲ ሳቢያ አሁንም ሀገራችን ከተመፅዋችነት መውጣት አልቻለችም።ይህ እንዳለ ሆኖ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የወያኔ መንግስት ለግብርና ምቹ የሚባለውን መሬት ለውጭ ሃገር ኢንቨስተሮች ተመጣጣኝ ባልሆነ ዋጋ ከመሸጡም ባሻገር ይህን የመሬት ወረራ ከምዕራቡ የሀገራችን ክፍል ጀምሮ አሁን ደግሞ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ያሸጋገረው ሲሆን በዚህም ምክንያት የሚፈናቀሉ ዜጎች ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ የመጣ ሲሆን ሃገራችንም በምግብ እህል ራሷን የምትችልበት ዕድል የጨለመ እንዲሆን አድርጓታል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በምግብ እህል ራሷን እንድትችልና ከምንታወቅበት ረሃብ ነፃ ለመሆን የሚከተሉት ነጥቦች መስተካከል ይኖርባቸዋል።

1. የወያኔ የመሬት ፖሊሲ መቀየር ይኖርበታል፤
2. የመሬት ወረራው መቆም አለበት።

ከላይ የተመለከቱት ሁለት ነጥቦች እስካልተስተካከሉ ድረስ በየዓመቱ በሚሊየን የሚቆጠሩ ዜጎቻችን በረሃብ ከመርገፋቸውም ባሻገር ሀገራችንም በጊዜ ሂደት በእጅ አዙር ቅኝ ገዢዎች እጅ መውደቋ አይቀርም።ስለሆነም የዚህ ሁሉ ችግር መንስኤ የሆነውን የወያኔ መንግስት ታግለን እንድንጥል በጋራ ለመነሳት ጊዜው አሁን ነው።

# ፈጣኑ ሎተሪ ሲፋቅ ያው ነው

**Betelehem Gedle/Hof**

በአዲሱ ዘመን ኢትዮጵያውያን ትልቅ ዕረፍት አገኘን በማለት እየተናገሩ ስለአዲሱ ዘመን ደግሞ የሰጠን ፈጣን ሎተሪ ያው እንደበፊቱ ቢፍቁት ባዶ እና የተጭበረበረ ነው።ለምስኪኑ ሰፊ ህዝብ የማይወጣ የድብብቆሽ ሎተሪ ለወያኔና ለወያኔ መሰሎቹ ብቻ የሚወጣ ሎተሪ ሌላውን የማያካትት ቁማር መሆኑ ኢትዮጵያውያንን እያሳሰበ ሄዷል።

እናንተዬ አንዱን ነቀርሳ ስንገላገል መጪው ሞኝ የመሰለ ነቀርሳ በቦታው ይቀመጣል።ስለዚህ አዲሱ ነቀርሳ አመራሮችን ከአሁኑ ቢያሻሽሉ መልካም ይመስለኛል።እምቢ ካሉ ግን በመጀመሪያ የተሰጥዎትን የቢጫ ካርድ ወደቀይ ለመቀየር ተዘጋጅተናል።እና ያስቡበት።ይድረስ ለአቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ።

# በህዝብ ላይ የሚደርሰው መረን የለቀቀ ጭቆና እስከ መቼ?

**Tigist Abate/Germany**

በህዝብ ላይ የሚደርሰው መረን የለቀቀ ጭቆና የሚያከትምበትን ሰዓትና ደቂቃ በትክክል ማወቅ ቢያስቸግርም ለግፈኞች ውድቀት ምክንያት ምን እንደሆነ ማወቅ ግን አስቸጋሪ አይደለም፤ነገር ግን እስከ መቼ ድረስ......? ከድሮ እስከ አሁን በአገራችን ኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ቆመን ስናስብ በእጅጉ የሚያሳዝንና ከነበረው ሁኔታ የሚተናነስ አይሆንም።ደርግም የመንግስትን በትረ-ስልጣን ጨብጦ ፍፁም ፈላጭ ቆራጭ በመሆን የኢትዮጵያን ህዝብ መብት በመግፈፍ ያስተዳደር በደልን በተደጋጋሚ በማድረሱ ግብዓተ መሬቱን አፋጥኖ በመጨረሻውም እስከ ወዲያኛው ተገረሰሰ።

አሁንም ያ በኢትዮጵያ የምንኖር ብሄረሰቦች /ጎሳዎች ሁሉ ከብዝሃነታችን በላይ አብሮነታችን ውህደታችን ገላጭ ክብርና ሞገስ ከመሆኑም ባሻገር የአንድነታችን የቃል ኪዳን ማህደር መገለጫ በመሆኑ አገራችን ለረጅም ዘመን የብሄረሰቦች ታሪክ ባለቤት ሆና ቆይታለች። በአንፃሩ ይህ ውበታችን ለወያኔ የዘረኝነትና የብሄረሰቦች መከፋፈል አደጋ ተጋልጦ ለአንድ አገር ትልቅ የኢኮኖሚ የፖለቲካ የማህበራዊ ውድቀት መሆኑን አመላክቷል።እንዲሁም ስርዓቱ የህዝብ ድጋፍ ስለሌለው የጥቂት ባለስልጣናት ጥቅም ማካበቻና የአገር ሃብት መበዝበዣ ሆኗል።

ስለዚህ እነዚህን አሳሳቢ ጉዳዮች እስካሁን እንዴት.........?እስከ መቼ........? የሚለውን ለመመለስ የኢትዮጵያ ህዝቦች በጋራ ሆነን ነፃነታችንን ለማረጋገጥና በህዝባችን ላይ የሚደርሰውን ጭቆና ለማስቆም በያለንበት ልንረባረብ ይገባል።

# የደም ውርስ

**Yared Tadese Abraham/Hof**

መለስ ዜናዊ በስልጣን በነበረበት ወቅት የወያኔ መንግስት ከሚታወቅበት እና ከሚወቀስበት ጉዳይ አንዱ ድምፃችን ይሰማ በማለት ለሰላማዊ ተቃውሞ አደባባይ በሚወጡ ዜጎች ላይ በመሳሪያ ኃይል የሞት እርምጃ መውሰዱ ሲሆን

ለምሳሌም በ1987 እና በ1993 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ እንዲሁም ምርጫ-97ን ተከትሎ በአዲስ አበባ ነዋሪዎች ላይ የተፈፀመው የጅምላ ግድያ በአይነቱ የሚጠቀስ ነው።

ይሁንና የመለስ ዜናዊ ሞት ተከትሎ አዲስ ጠቅላይ ሚንስትር ቢሾምም ይህ ለሰላማዊ ተቃውሞ በሚወጡ ዜጎች ላይ የሚፈጸመው የግድያ እርምጃ የቀጠለ ሲሆን እ.ኤ.አ. በኦክቶበር 2012 በደቡብ ወሎ በአራት ንፁሐን ዜጎች ላይ የተፈጸመው ግድያ አይነተኛ ምሳሌ ነው።

በእርግጥ የሥርዓቱ አመራሮች ደጋግመው እንዳረጋገጡልን የመለስ ሞት በወያኔ አቋም እና ፖሊሲ ላይ ምንም ለውጥ ያላመጣ ሲሆን የነበረው አፈና፤ግድያ እና ጭቆና እንደቀጠለ ይገኛል።በመሆኑም ይህን አፋኝ እና በንፁሐን ደም የተጨማለቀ ስርዓት ማስወገድ የሁላችንም ኃላፊነት ይሆናል።

# የወያኔ ስራዎች

**Hiwot Tilahun/Zeil**

በፀረ ዴሞክራሲያውያንና ስብዕና ባልተሞላባቸው የወያኔ ፓርቲና አሸከሮቻቸው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያኖች በችግር በመከራ ብሎም በከፋ የህግ ስርዓት እየተመራን መኖር ከጀመርን ድፍን 22 ዓመታት አስቆጥረናል።በዚህም ረጅም የአገዛዝ ዕድሜዎች ብዙ የንፁሃን ደም በከንቱ ፈሷል። በተለይ በምርጫ 1997 ዓ.ም ወያኔ ሙሉ ለሙሉ በመሸነፉ ስልጣን ላለመልቀቅ ምርጫውን አጭበርብሯል።በዚህ በተጭበረበረ ምርጫ የኢትዮጵያ ህዝብ ባለመስማማቱ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ ቢያደርግም የብዙ ንፁህ ሰዎች ደም በከንቱ ፈሷል።

ከዚህ የወያኔ ፓርቲ አምባገነናዊና ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ ለመሸሽ በሱዳን በሰሃራ በረሃና በሜዲትራኒያን ባህር ላይ ህይወታቸውን ያጡ ንፁሃን ዜጎች ቤት ይቁጠረው።

ሌላው በጣም አሳዛኙ ደግሞ በሚዲያና በጋዜጠኞች ላይ እየደረሰ ያለው ስብዕና ያልተሞላበት ግፍ ያዘለ ስቃይ እስካሁን ድረስ መቀጠሉና በአገሪቱ የመናገርና በነፃነት ሃሳብን የመግለፅ መብት መታፈኑ አገር ያወቀው ፀሃይ የሞቀው ጉዳይ መሆኑ ነው።

በቅርቡ የዚህ ሁሉ ችግር ፈጣሪ ባለቤት የወያኔ ፓርቲ ቁንጮ የህግ አውጪና አስፈፃሚው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እንደሆነ ተረጋግጧል።ይህ ጠቅላይ ሚኒስትር በሞት ቢለይም የስልጣን ቦታውን ለህወሓት ፓርቲ ታማኝና ከጨካኝ ልጆች ውስጥ ተመርጦ ከስልጣን ወንበሩ እንዲቀመጥ ተደርጓል።አሁንም ጠ/ሚኒስትር ሃይለማርያም ይህንን አምባገነንነትና የፀረ-ዴሞክራሲ አገዛዝ እያራመዱ ይገኛሉ።እኔም ይህንን ፓርቲና ስርዓት ለመገርሰስ ታጥቀን እንነሳ ስል አገራዊና ወገናዊ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

# ድህረ-መለስ አፈና በኢትዮጵያ

**Abebe Demelash/Hof**

የመለስ ዜናዊ ሞት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ የተወሰነ አዎንታዊ ለውጥ ያመጣ ይሆናል ተብሎ ቢጠበቅም በተግባር እየታየ ያለው ግን የአፈናው ሥርዓት ከጊዜ ወደጊዜ እየከፋ የመጣ ሲሆን በተለይም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ነጥቦች መመልከት የሥርዓቱን ፍፁም አምባገነናዊነት አጉልቶ ያሳየናል።

1. ነፃ ፕሬስን መከልከል፡-በኢትዮጵያ የመለስ ዜናዊን ሞት ተከትሎ ፍትህ ጋዜጣ እና ፍኖተ ነፃነት በመባል የሚታወቁ የነፃው ፕሬስ ጋዜጦች ሙሉ በሙሉ ከህትመት የታገዱ ሲሆን ይህ የወያኔ አምባገነናዊ ድርጊት በኢትዮጵያ ይታይ የነበረውን የነፃ ሚዲያ ተስፋ ሙሉ በሙሉ ያጨለመ ከመሆኑ ባሻገር የዜጎችን ሃሳባቸውን በነጻነት የመግለፅ መብታቸውንም የገፈፈ ድርጊት ሆኖ እናገኘዋለን።

2. የዜጎች ያለአግባብ መታሰር፡-በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ያለአግባብ የሚታሰሩት ዜጎች ቁጥር እጅግ ከመብዛቱ የተነሳ የወያኔ መንግስት ተጨማሪ ወህኒ ቤቶችን ያስገነባ ሲሆን በተለይ የመንግስትን በሃይማኖት ጣልቃ ገብነትን በሰላማዊ መንገድ የተቃወሙትን እንዲሁም የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን በማዋከብ፤በማስፈራራት እና ያለበቂ ማስረጃ ለረጅም ጊዜ በማሰር እና በማሰቃየት ላይ ይገኛል።

የሲቪክ ማህበራትን መዝጋት፡-የኃ/ ማርያም አስተዳደር በቅርቡ ከስምንት በላይ የሚሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ የሲቪክ ማህበራትን የዘጋ ሲሆን በተለይ እነዚህ የሲቪክ ተቋማት በሃገሪቱ ወጥ በተለይም በማህበረሰቡ ውስጥ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ንቃተ-ኅሊናን በማዳበርና ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ አንፃር ያበረከቱ ከነበረው ወሳኝ ሚና አንፃር የነዚህ ተቋማት መዘጋት ወደፊት የሚያስከትለው ተጽዕኖ ቀላል የሚባል አይሆንም።

ከላይ በሶስት ነጥቦች እንዳየነው የግለሰብ ለውጥ በስርዓቱ ላይ ያመጣው አንዳችም የለውጥ አዝማሚያ ያለመኖሩን ነው። በመሆኑም በሀገራችንና በዜጎቿ ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍና መከራ ማቆም የሚቻለው ስርዓቱን ሳንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ታግለን ስንጥለው ብቻ ነው።በመሆኑም ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ በጋራ እንነሳ።

# የዜግነት ግዴታችንን በጋራ እንወጣ

**Berhanu Bayu/Schweinfurt**

ህዝብ አማራጭ ሃሳቦችን ይፈልጋል።ጠንካራ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም ድርጅቶች ሳይኖሩ ጠንካራ ዴሞክራሲ እውን ለማድረግ አስቸጋሪ ነው።በቅርቡ አዲስ የተመረጠው ጠቅላይ ሚንስትር ኃ/ማርያም ደሳለኝ የወያኔ የከፋት ወንበር ላይ መቀመጡ የሚገርመን አይደለም።ድሮም አውታንቲ ሾፌር ይሆናል።ግን መኪናውም መንገዱም ያው ነው።ምኑ ላይ ነው ለውጥነቱ ወይም ተስፋነቱ?እንግዲህ ለውጥ እንዴት ከነሱ መጠበቅ ይቻላል?

አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር የወያኔ ሽፋን የሆነ መጋረጃ ነው።አሁን ግን ለሚያየው ሰው እንደድሮው ጠቅላይ ሚኒስትር በትዕቢት የሚያስብና የሚሰራ አይመስልም እውነተኛው ጠቅላይ ሚንስትር ግን ከዚህ በስተጀርባ ያለው በመለስ ``ክሎን`` የተደረገ ገጽታ ነው።

እውነተኛው ኃ/ማርያም ከትግራይ ያልበቀለና በሕወሃት የታቀፈ ስንግ ወያኔ ነው።የልቡ ሀሳብና ምኞት ሁሉ ከወያኔ ጋር ልክክ ብሎ አንድ የሆነ ነው።የድሮው ጠቅላይ ሚንስትር የመረጠውና ያቀፈው በዚሁ አድርባይ ባህሪው ነው።

ድርጊቱ ከወያኔ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ህዝብ የሆነ ለግለሰቦችና ለህወሀት አባላት የቆመ ነው እንጂ ለሀገርና ለወገን የቆመ አይደለም።ስለዚህ በሀገራችን የህግ የበላይነትና የፍርድ ነፃነት እውን እንዲሆን ልንታገል ይገባል። በአጠቃላይ የወያኔና የገዢው ፓርቲ በፈፀሟቸው ጥፋቶች የደረሰብንን ጥፋት ከግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም ስለፈጠራቸው እጅግ

አሰቃቂ ክስተቶች ተጠያቂ ለማድረግ የዜግነት ግዴታችንን በህብረት ሆነን መወጣት ስንችል ብቻ ነው።ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!



# አቶ በረከት ስምዖን ምን ነካቸው ???

**Kidest Zelalem/Köln**

ኤርትራዊ ሆነው በኢትዮጵያ ከፍተኛ የስልጣን ሃላፊነት የተሸከሙት አቶ በረከት ስምዖን በኢትዮጵያ ላይ የሚፈርድ፣ዜጎችን የሚያሸማቅቅ፣ ለአገራቸው የተሰውትን የሚያናንቅና በተለይም በውድ አገራቸው የሚመኩ ወገኖችን የሚያኮስስ ንግግር ማድረጋቸው በህወሃት ነባር ታጋዮች ዘንድ ቅሬታ ማስነሳቱ ታወቀ። አቶ ስዬ አብርሃ፣አቶ ገብሩ አስራት፣እነ አቶ ተወልደን በስም በመጥራት በኤርትራ ጉዳይ ላይ ጥፋተኛ ያደረጉት አቶ በረከት “
አንድነትና አንድ አገር” የሻዕቢያ መዝሙር መሆኑን በመናገር ኢትዮጵያ ውስጥ መገንጠል ለሚፈልጉ ጊዜው ሲደርስ እንደ ኤርትራ መገንጠል መብታቸው መሆኑን ተናግረዋል።

በሚኒስትር ማዕረግ የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ሃላፊ አቶ በረከት ይህንን የተናገሩት Eritrean Oppositions Arabic Paltalk በሚሰኝ የኤርትራ ተቃዋሚዎች የፓልቶክ መወያያ ክፍል እንግዳ ሆነው ባካሄዱት የጥያቄና መልስ ነው።ከአጀማመሩ የሻዕቢያ ውልድ እንደሆነ የተነገረለት ሕወሓት ሲመሠረት ምልመላውንም ሆነ አመራሩን የሻዕቢያ ሰዎች እንደተቆጣጠሩት ሲነገር የኖረ ነው።

አቶ በረከት ይህንን ታሪካዊ የወያኔና የሻዕቢያ ትስስር ባልካደ መልኩ ነበር ቃለምልልሱን ያደረጉት። “በኢትዮጵያ ቅኝ ግዢ ተይዘናል” በሚል “ነጻነት” እንደሚፈልጉ ወስነው በነበሩ የኤርትራ ተወላጆች ላይ የተወሰደው ወደ አገራቸው የመመለስ ሂደት ፍጹም ስህተት እንደሆነ የተናገሩት አቶ በረከት፣በወቅቱ ለተወሰደው እርምጃ አቶ ስዬ አብርሃ፣አቶ ገብሩ አስራትና እነ አቶ ተወልደን ተጠያቂ አድርገዋል። ስህተቱንም አንድ ወቅት የተደረገ፣ካሁን በኋላ የማይደገም እንደሆነ ዋስትና ሰጥተዋል። አቶበረከት የከሰሷቸው የተጠቀሱት የቀድሞ የሕወሓት ባለስልጣናት ሟቹን አቶ መለስን በአገር ክህደት የወነጀሉና ሻዕቢያ መደምሰስ አለበት በማለት ቁርጠኛ አቋም በመያዝ በድርጅታቸው የታገሉ እንደነበሩ በብዙዎች ዘንድ አይዘነጋም።

ኤርትራ “ቅኝ ግዢ በቃኝ” ካለች በኋላ አመራሮቿ በኢትዮጵያ በተለያዩ መስኮች የንግድ ዝርፊያ ሲያካሂዱ እንደ ነበር በሰፊት የተወሳ ቢሆንም አቶ በረከት የሃሰት (ፎርጂድ) ዶላር በማተም፣ ቡናና ሰሊጥ “በኮንትሮባንድ” በማጋዝ ሲሰራ የነበረውን ሸፍጥ ጠቁመዋል። ኢትዮጵያ ላይ እንዲህ አይነቱ ሸፍጥ መሰራቱን ሲናገሩ ለምን የሻዕቢያ አመራሮችና ወኪሎቻቸው እንዳልተከለከሉ አላብራሩም። ይህ ህገወጥ ንግድ ለባድመ ወረራ ምክንያት መሆኑን ግን ጠቁመዋል። ከባድመ ወረራ ጀርባ የተለያዩ ችግሮች እንዳሉም አመላክተዋል።

ባድመ መሬቱ የኢትዮጵያ እንዳልሆነ ይታወቃል” በማለት የሚያስተዳድሯትን አገር በክህደት ጅራፍ እየገረፉ መናገራቸው ሁላችንንም ያሳዘነን የክፍለ-ዘመኑ አገራዊ ክህደት አይተናል።

ትክክለኛ ፍትህ ካለ ጋዜጠኞችንና የፖለቲካ ሰዎችን በአገር መክዳት ወንጀል ከሻዕቢያ ጋር አስተሳስሮ እስር ቤት ከማጎር በተረ-ስልጣኑን ይዘው የሚከዱት በረከት ስምኦን ሌላም ይገባቸው ነበር።እነዚህ ሰዎች የስንት ሰው ደም እንደ ዝናብ የፈሰሰበትን የባድመ ጉዳይ እንዲህ በዋዛ አሳልፈው በመስጠት ከሻዕቢያ ጋር ለማበር ዳዴ ማለታቸውን መላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሌሎቹ ቀልዶቻቸው በቸልታ የሚያልፈው አይሆንም።

የሆነ ሆኖ ግን እነዚህ ሰዎች አገራችንን በጣጥሰው ሳይሸነሽኗት መላው ሃይላችንን አሰባስበን ለስርዓቱ መለወጥ መስራት አለብን እላለሁ።እግዚያብሄር አገራችንን ይባርክልን!!!

# የፖለቲካ ፓርቲዎችና የመንግስት መዋቅሮች በኢትዮጵያ

**Eden Dawit Kidane/Gießen**

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ እየታየ ያለው የመንግስት መዋቅሮች መዘበራረቅና የፖለቲካ ፓርቲዎች የራሳቸው ፕሮግራምና አፈፃፀሞች በብቃትና በጥራት ሊያካሂዱ በማይችሉበት ሁኔታ ላይ ደርሰዋል።የፓርቲና የመንግስት መዋቅሮች መለየት ሲገባቸው በመንግስት ተፅዕኖ ስር እንዲገቡ እየተደረገ ይገኛል።በኢትዮጵያ ፓርቲዎችና የመንግስት መዋቅሮች አንድ በመሆናቸው የገዢው ፓርቲ ፍላጎትና ምኞት በመንግስት መዋቅሮች ውስጥ ተካቶ በአገሪቱ የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ የበላይነትና አምባገነንነት እንዲሰፍን አድርጎታል።በዚህ ሁኔታ በአገሪቱ የሚገኙ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ድምፅ አልባ መሳሪያ ሆነዋል።

አሁን ባለው ሁኔታ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ለህዝባቸው የተሻለ የፖለቲካ አማራጭ ማውጣት ቀርቶ በብቃት መንቀሳቀስ እየተሳናቸው መጥተዋል።በዚህም ምክንያት ህዝብ አማራጭ መንገዶችን እንዳያይ በጨለማ ውስጥ እንዲኖር ተገዷል።የአገራችን ህዝቦች አማራጭ ወይም ተስፋ አድርገው የሚፅናኑበት መንገድ አንደኛ በውጭ የሚኖረውን ዜጋ የህዝቡን ጭቆናና በደል ለአለም እንድናስማለትና በትግሉ እንድናግዘው ነው።

ታዲያ እኛ ምን እያደረግን ይሆን? ለህዝባችን በአንድ ድምፅ ቃል ልንገባለት ይገባል።ትግላችንን ቀጥለን ይህንን አምባገነን የኢህአዴግ መንግስት ልናስወግደው ይገባል።ህዝቡ ነፃነት ተጠምቷል።የአገራችንን ህዝቦች ከእኛ የሚፈልጉትን ድጋፍ ለመስጠት ኢህአፓም ከጎናችን ነው።ኢትዮጵያን እግዚያብሄር ይባርክ!!!

# በኢትዮጵያ ፍትሐዊ የሃብት ክፍፍል እንዳይኖር የተደቀነው እንቅፋት!!!

**Dawit Fanta /Eng./Germany**

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከዕዝ ኢኮኖሚ ተላቃ ገበያ መር ኢኮኖሚ እየተከተለች ነው ከተባለ ከሁለት አሰርት ዓመታት በላይ ቢሆንም በማህበረሰቡ ውስጥ እየታየ ያለው የሃብት ክፍፍል ግን ፍጹም ገበያ መር ኢኮኖሚ ከሚያስከትለው ተጽዕኖ ተመጣጣኝ ካለመሆኑ ባሻገር በሃገሪቱ ውስጥም እየታየ ነው የሚባለው “ዕድገት“ የጥቂት ቡድኖች ዕድገት ሆኖ እናገኘዋለን። በመሆኑም በሃገሪቱ ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ ለመጣው ድህነትና ኢ-ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ዐይነተኛ ሚና እየተጫወቱ የሚገኙትን ጉዳዮችን መዳሰስ የዚህ ፅሁፍ ቀዳሚ አላማ ይሆናል።

1. **የፖለቲካ ተቋማት አወቃቀር / The Nature of Political Institutions/:-** በግልፅ እንደሚታየው የወያኔ መንግስት የሃገሪቷን የፖለቲካ ተቋማት ያዋቀረበት መንገድ ሁሉን አሳታፊ / Inclusive/ ያልሆነ ይልቁንም ጥቂት የአንድ አካባቢ ተወላጅ ኅሩያን /Elites/ በዋናነት የሚያሽከረክሩት መዝባሪ ተፈጥሮ / Extractive Nature/ ያለው ሆኖ እናገኘዋለን።ይህ አይነቱ የፖለቲካ ተቋማት አደረጃጀት በባህሪው እውነተኛ መድብለ ፓርቲ /Bona fide Pluralism/ እንዳይፈጠር በግልጽም ይሁን በህቡዕ / Overtly or Coverly/ ስለሚከላከል ተጠያቂነት የሌለበት ገደብ አልባ ሥልጣን /Unconstrained Power/ በጥቂት ኅሩያን እጅ በህግ ላልተገደበ ጊዜ እንዲቆይ ያደርገዋል።ይህም መዝባሪ የፖለቲካ ተቋም ለሀገር እና ለህዝብ ዘለቄታዊ ጥቅም ከመስራት ይልቅ የጥቂት ቡድኖችን ሥልጣን ለማጠናከሪያነት የሚረዱ አቻ መዝባሪ የኢኮኖሚ ተቋማትን /Extractive Economic Institutions/ በመገንባት ላይ ይወሰናል።ከዚህም ባሻገር የስርዐቱ ዋነኛ አጀንዳ የፖለቲካ ሥልጣኑን ማስጠበቅ በመሆኑ የሀገሪቱን አብዛኛ መዋዕለ ነዋይ ህዝብን ለማፈን የተጋነነ የፖሊስ ኃይልን እና የደህንነት ተቋማትን በመገንባት፣በካድሬ ምልመላ እና ስልጠና እንዲሁም በድርጅታዊ ተግባራት ላይ ስለሚያውለው በስርዐቱ ዙሪያ ካሉ ጥቂቶች ውጪ ያለው ሰፊው የህብረተሰብ ክፍል ለገኘዎቹ የሀብት ምንጭ ከመሆን በዘለለ የሃገሪቱ የሀብት ተካፋይ ሊሆን አይችልም።በተጨማሪም በዚህ ዓይነት የፖለቲካ ስርዐት ውስጥ በሙስና ላይ የሚኖረው ተጠያቂነት ለዘብተኛ በመሆኑ ከግለሰብ ጀምሮ እስከተደራጀ የሙስና ወንጀል መመልከት የተለመደ ተግባር ይሆናል።ለዚህም ነው በኢትዮጵያ የሚገኙ የፖለቲካ እና የጦር ሹመኞች የሀገሪቱን ሀብት በመዝረፍ እና በማሸሽ ተግባር የተጠመዱት።

**የኢኮኖሚ ተቋማት አወቃቀር /The Nature of Economic Institutions/:-**በኢትዮጵያ ያለው የኢኮኖሚ ተቋማት አወቃቀር በዋናነት በሥልጣን ላይ ላለው ቡድን ተጨማሪ ኃይልን በሚፈጥር መልኩ መዝባሪ ባህርይ /Extractive Nature/ ያለው ሲሆን የሀገሪቱ የተፈጥሮ ሃብትም ከሞላ ጎደል በዚህ ቡድንና በሥልጣኑ ዙሪያ ባሉ የጥቅም ተሳሳሪዎች / Cronies/ እጅ ይገኛል። በአሁኑ ጊዜም ከፍተኛ ብዥታ እየፈጠረ ያለው የእዚህ አናሳ ቡድንና በሥልጣኑ ዙሪያ ያሉ ጥቅመኞችን የሀብት ዕድገት የመላው ህብረተሰብ እና የሀገሪቱ ዕድገት አስመስሎ የማቅረቡ ጉዳይ ነው።

በመሰረቱ መዝባሪ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ተቋማት እርስ በእርሳቸው ተመጋጋቢ ሲሆኑ እንዲህ አይነቱ የፖለቲካ ተቋም ሥልጣንን ያለገደብ በጥቂቶች እጅ በማድረግ አቻ የሆኑ የኢኮኖሚ ተቋማትን ለመፍጠር፣የኢኮኖሚ ተቋማቱን በተለየ ሁኔታ ተጠቃሚ የሚያደርጉ ህጎችንና አዋጆችን ለማፅደቅ፣በገበያው ላይ ተጽዕኖ ለመፍጠር፣ነጻ ፉክክር እንዳይኖር እንቅፋቶችን ለመፍጠር /To erect entry barriers/ ሲረዳ በምላሹ እነዚህ መዝባሪ የኢኮኖሚ ተቋማት የሀገሪቱን ሀብት ከአብዛኛው ህዝብ በመዝረፍ በሥልጣን ላይ ያለውን ቡድን በሀብት እና ኃይል ይበልጥ እንዲጠናከር ያደርጉታል።

ለዚህም አይነተኛ ማሳያ የሚሆነን የህወሃት ቡድን የፖለቲካ ሥልጣኑን ያለገደብ ሲቆጣጠር “ኤፈርት“ የሚባል መዝባሪ ግዙፍ የንግድ ኢምፓየር የገነባ ሲሆን ከኤፈርት የተረፈውን ክፍተት የፖለቲካ እና የጦር ባለስልጣናት እንዲሁም በሥርዓቱ ዙሪያ የሰፈሩት ጥቅመኞች በግላቸው እና በዘመዶቻቸው ስም ባስመዘገቧቸው የንግድ ተቋማት ስልጣንን ተገን ያደረገ ካፒታሊዝም / Crony Capitalism/ መመስረት ችለዋል።በመሆኑም የወያኔ መንግስት በየጊዜው የሚያወጣቸው ባለሁለት አሃዝ “ዕድገት“ በእርግጥም የኢትዮጵያ ዕድገት ሳይሆን የእነዚህ ጥቂት ቡድኖች ግዙፍ የንግድ ተቋማት እድገት ሆኖ እናገኘዋለን።

በመሆኑም በኢትዮጵያ ውስጥ ፍትህዊ የሃብት ክፍፍል ሊመጣ የሚችለው በሃገሪቱ ያሉ የፖለቲካም ሆኑ የኢኮኖሚ ተቋማት ከመዝባሪነት ወደ ሁሉን አቀፍነት እስከተቀየሩ ብቻ ይሆናል።ለዚህም፡-

1. የፖለቲካ ተቋማቱ እውነተኛ መድብለ ፓርቲ እንዲኖር መፍቀድ ይኖርባቸዋል። ይኸውም ሥልጣን በጥቂቶች እጅ ብቻ እንዳይቀር ከመርዳቱም ባሻገር ሥልጣን በህገ-መንግስት በተገደበበት ሁኔታ ለባለድርሻ አካላት እንዲከፋፈል ይረዳል።
2. ነጻ የመገናኛ ብዙኃን መበረታታት ይኖርባቸዋል፥የሃገሪቱ የፍትህ ሥርዓት ለፍትህ ብቻ መቆም ይኖርባቸዋል፥እንዲሁም በሃገሪቱ የሚወጡ ህጎች፣አዋጆች እና ደንቦች ለሁሉም ዜጋ እና ተቋማት እኩል ዕድል የሚፈጥሩ መሆን ይኖርባቸዋል።
3. በሃገሪቱ እውነተኛ ነጻ ገበያ እና ነጻ ንግድ እንዲኖር መንግስትም ሆነ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከንግድ መውጣት ይኖርባቸዋል።በእጃቸው የሚገኙ ተቋማትም መንግስት በጊዜያዊነት እንዲረከባቸው በሂደት ግን በፕራይቬታይዜሽን ህግ መሠረት ወደግል ይዞታነት እንዲዛወሩ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራዊ ለማድረግ የወያኔ መንግስት “በሬሳዬ ላይ“ ማለቱ የማይቀር ነው።ይህም ማለት ይህ ጠባብ የአናሳዎች ቡድን በኃይልም ቢሆን እስካልተሸነፈ ድረስ እጅግ የሚበዛው የኢትዮጵያ ህዝብ “የበይ ተመልካች“ ሆኖ በአስከፊ ድህነት እንዲኖር ይገደዳል።የወያኔ ባለስልጣናትም የግላቸውን እና የቡድን ዕድገታቸውን የሃገሪቱ እና የሰፊው ህዝብ ዕድገት አስመስለው የሚያቀርቡትን ድራማ ይቀጥሉበታል።




ገዳማትን አትኩ እጅግ ጥቂት እጅግ ብዙ ነኝ...
ገለአልጣናትና ለሆዱ ያደረ እቅመ ቢስ...
የማያቋርጡት የሞት ገደል...
ማን ይሆን ገለጎምቱ ተረኛ...

# Woyane is still cheating the world!

**Tigist Belayneh Zeray /Alsfeld**

Who knows the whereabouts of Dictator Meles Zenawi? Meles' sickness is just exhaustion and he is taking extended vacation, then why Bereket and etal are discharging contradictory information to their loyal media outlets? Why is he spending that much time in foreign land while he could take the so called deserved vacation in Ethiopia itself? The truth of the matter is Meles is very ill and had a critical surgery and Bereket and et al are praying that his situation improves sooner than later. There is no doubt that Meles is indeed alive but his return to his job is very unlikely.

